አስቸኳይ ግልጽ ደብዳቤ

ሚያዝያ 1 2001

# የአክራሪ ሙስሊሞች መግደል...ማባባሱ ካልተገታ ማጠፊያውን ሊያሳጥር ይችላል!

ለተከበሩ ሼክ. ዶር. መሓመድ አል አሙዲ
ባሉበት፦

የኢትዮጵያዊ የስጋት ሰላምታዬ ይድረስልኝ

በአክራሪ ሙስሊሞች ምክንያት በአገራችን ከግራኝ በኋላ ታይቶ-ተሰምቶ የማይታወቅ አደገኛ ገጹን ካሳየበት ከ18 ዘመናት ጀምሮ እየከፋ እየተስፋፋ በመምጣቱ ወገናዊ ስጋቴን መግልጽ ግዴታየ ነው፡፡ ግድያው፤-ዝርፊያው ዉርደቱ የደረሰው በክርስቲያኖች ላይ ብቻ ነው።

የተከበሩ ሼክ አል አሙዲ፦ እርስዎም የስጋቱ ይባስም የጭንቀቱ ተካፋይ ይኾናሉ በማለት እነሆ ላካፍልዎ ወደድሁ። ባላዋቂዎች ዘንድ እንደበግ እንደሞኝ እንደፈሪ ሊያስገምታቸው ይችላል። “በግ ከበረረ፡ ሞኝ ካመረረ” የሚለውን ማስታወስ ግን አይችሉም። “ የፈሪ በትር ሆድ ይቀስር “ የሚለውንም አለመርሳት አይጎዳም።

ከኹሉም በላይ ግን በኢትዮጵያችን ውስጥ ከጥንት የተወረሰውን በኹለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የነበረው አኩሪ ፍቅራችን ከ45-50 ዓመታት ዕድሜ በላይ ባሉት ሙስሊም ወገኖቻችን ዘንድ እንዳለ መኾኑን መረዳት ከስሜታዊ ስህተቶች ያድን ይመስለኛል።
ትንሽ ላብራራው፦የገዳዮቹ፦ እንዲያውም በአጠቃላይ የወንጀለኞቹ ወላጆች፦ አጎት አክስቶች...እተጎዱት ወዳጅ ዘመዶቻቸው ዘንድ ሄደው እንደድሮው አልቅሰው፡ አጽናንተው የእዝናቸውን ደግሰው አስተናግደው በሃዘነተኝነት ይቀመጣሉ። የተቃጠለባቸውን አብረው ሠርተው ለተዘረፈባቸው ከብትም ኾነ ንብረት ረጥበው ሙስሊሞች ከወገኖቻቸው የዚህ ስቃይ ተሳታፊዎች ናቸው። በይበልጥም በዳዮቹ ልጆቻቸው በመኾናቸው ሃዘኑ-ፀፀቱ የበለጠ ይጎዳቸዋል። በዚህ ዓይነት ኹናቴ ክርስቲያኑ የሚበቀለው እማን ላይ ነው? በወንድማማቾች መኻል የኹለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች እንዳሉ አናውቅም?

የተከበሩ ሼኩ ( እባክዎ ይፍቀዱልኝ “ሼኩ” ብዬ እንድቀጥል ጊዜ ይቆጥብልልኛልና!)

ስለዚህ ጉዳይ ልጽፍ ሳስብ ከወዳጆች ርዳታ በማግኘት ከኹለቱም ቅዱሳት መጽሓፍት በማጣቀስ ሳይደርሱበት ከሰለምህ ትጸድቃለህ አልያም ትኮነናለህ እያሉ መግደል ለራስ ኩነኔን ማትረፍ መኾኑን በማሳየት ሙስሊም ልጆቹን ከምድራዊ ወንጀለኝነትና ከሰማያዊ ኃጢአት፤ አገራችንንም ከጥፋት ወገናችንን ከዕልቂት ለማዳን እሞክራለሁ ብዬ ስዘጋጅ፦

የርስዎን " ከታዲያስ አዲስ " ጋር ያደረጉትን ቃለ-ምልልስ ስሰማ ሽክሜ ተቃለለልኝ። ከቅዱሳን መስሓፍትም ኾነ፤ የደረሱትን ዕልቂቶች ከመዘርዘር አድኖኛልና! ይበልጥም ፈቃደኛ ከኾኑ ዝቅ ሲሉ እንደሚያገኙት እሳቱን ሊያጠፉ ይችላሉና!
የተከበሩ ሼኩ እኔ በስንት ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምገኘው የት የት ገዳማት፤- ቤተ ክርስቲያች እንደተዘረፉ/ተቃጠሉ፦ በየት በየትስ ክርስቲያኖች እንደተገደሉ በከፊልም ቢኾን ሳውቅ ንብረታቸውንም እንደተዘረፉ ስሰማ፡ ርስዎን መኻሉ ኾነው አያውቁም ማለት የራሴን አለማወቅ ማወጅ ይኾንብኛል።

የኹለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች ከስልምና ሃይማኖት መጀመርያ አንስቶ ከአንድ ጊዜ ( ግራኝ) በስተቀር በሰላም በመደጋገፍ በኑሯቸው ኹሉ በመረዳዳት ጠላትም ሲመጣ በአንድ በመመከት ዓለምን ያስደነቀ ትብብራቸው ለአብነትም ይነገር የነበረ መኾኑን ስንዘከር ትብብራቸውን ለማደፍረስ ያልምከረ "ኃይል" እንዳልነበረ ሳይጠቅሱ ማልፍ ግን ታሪክን መቀናነስ ይኾናል። ጣሊያንና እንግሊዝን ጠቀስ አርገን ወደ ሳውዲና ግብጽ እንዲሁም ሱዳን ስንመጣ ግፊቱ የበዛ እንደነበረ ዕድሜ የሰጠው ኹሉ ሳያውቀው አይቀርም። ናሲር በተነሳና በገነንበት ወቅት ሙስሊሞችን በያለበት ሊያነሳሳ እንደሞከረ ሲታወቅ በኢትዮጵያችን ላይ ግን ጥረቱ ጥቂት አልነበርም ቢባል አይጋነንም።

ኢትዮጵያችን ውስጥ በተለይ የናስርን ተንኮል እንዴት እንዳከሸፉት መስማቱ ልብ-ወለድ መጽሓፍ እንደማንበብ ነው። በ1950 ዓ.ም ለሃጅ የሄዱ ሙስሊም ወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመባቸውን የአገር ማስከዳት ሙከራ ሄደው ከተመለሱት መስማቱ ይዘገንን ነበር። " ለፀሎት ብለን ሄደን ከሙግትና ከጦርነት ያላነሰ ትግል ውስጥ ከረምን ያሉትን የአብሬቱን ሼክ በአክብሮት አስታውሳቸዋለሁ። ኾኖም " ሃይማኖት የግል አገር የጋራ" ነቱን የሚያምኑ ወንድሞቻችን ብዙሃኑ በነበሩብት ረግተው ሲመለሱ አንዳንዶች መገዛታቸው አልቀረም ነበር። ይህ ግን በመንግሥቱ ጽናትና በሕዝቡም በደም በሥጋ መተሳሩ ሙከራቸው ፋይዳ አልነበረውም። ለእኔ፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ጥልቀትና ዐዋቂነት ከሚያሳዩት ብዙዎች አንዱ ንጉሥ ሳውድ ለመጀመሪያ ጊዜ አገራችንን ሲጎበኙና ኹለቱ ነገሥታት ተዝናንተው ሲጫወቱ ጎብኚው  አቅሱም ውስጥ መስጊድ እንዲሠሩ ይፈቅዱላቸው ዘንድ ጠየቁ። ጃንሆይም ያላንዳች ማቅማማት " ምን ከፋን ደስ ይለናል" ማለታቸው ጎብኛቸውን አስፈነደቃቸው አስደነቃቸውም ይባላል። ከግለቱ መለስ ሲሉ ጃንሆይ " እርስዎም እንግዲህ ሜካና መዲና ላይ ቤተክርስቲያኖች እንድንሠራ ይፈቅዱልናል" ብለው አክሱም ላይ መስጊድ የመሥራቱ ነገር እስከ ቅርብ ጊዜ ተቀብሮ ቆይቶ ነበር።

ታሪክ ካነሳሳን ዘንድ አንድ ቀደም ካለ ሌላው ደግሞ ከቅርብ እንዳነሳ ይፍቀዱልኝ፤የመጀመሪያው አጼ ተዎድሮስ ለአንድ ጎብኚ ብሩን ወርቁን የዝሆን ጥርሱን ወዘተ ሸልመው እንዲሸኝ ለታዘዘው አሽከር የሰጡት ጥብቅ ትዕዛዝ ነበር፤፡ ሳያውቁት ባይቀርም ላስታውስዎ። ጎብኚው መርከብ ላይ ሲወጣ ሸኚው መጫሚያውን አውልቆ እንዲያጥበው ነበር። ግራ የገባው የንጉሥ አሽከር ሲመለስ ትዕዛዙን መፈጸሙን ለመንገር ገባ ። መጫሚያ እንዲያጥብ የታዘዘበት ምክንያትም እንዳልገባው ገለጸ። አባ ታጠቅም " ያገሬን አፈር ይዞ እንዳይሄድ ንው" ሲሉ ምሥጢሩ ያልገባው ሎሌ " ወርቁን ብሩን ...ኹሉ ሰጥተውት ለአቧራ!" ቢላቸው የሰጡት መልስ እንደማይዘነጋዎ ተስፋ ባደርገም ( በዚያን

ጊዜ ለነበረው ኹሉ የማይረሳ ትምሕርት ነበርና!) የአገሬ አፈር ከብርም ከወርቅም በላይ ነው።”

አበው ነገር በምሳሌ ይሉ አልነበረ? አንድ ልጨምር። ወደኋላ ኹሉም ይያያዛል! ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለፍርድ ቀርበው በነበሩበት ወቅት የራስ አበበ ስም ሲነሳ ወደ ልጆቻቸው ዘወር ብለው፦” ክቡርነታቸው እንኳን የሚገደሉ የሚሞቱ ሰው ነበሩ። ግን
<u>ዕውን የክቡርነታቸው ብኀይወት መቆየት በዚህ መንግሥት የሚፈለግ ነበር?” አሉ</u>

አኹን ወደ ቃለ-ምልልስዎ ልሂድ በዕውነት ልብ የሚነካ ነበር በተለይም ለእናት አገርዎ ያለዎትን ፍቅር ሲገልጹ፦”ውጭ አገር መዋዕለ-ንዋዬን ሳፈስስ በአንኀሌ አገሬ ውስጥ ግን በልቤ ነው” ያሉትን ሲያብራሩ የውጪውን ለትርፍ የአገርን ግን ወገንን ከችግር ከችጋር ለማላቀቅና በድህነት መጠራትንም ለማስቀረት እንደኾነ አስረግጠው ተናግረዋል። የርስዎን ለዛና ስሜት የተመላበትን አነጋገር ጽሑፌ ባያንጸባርቅ ቅር እንደማይሰኙብኝ ተስፋ አለኝ። “ አደራ አለብኝም” ብለው ነበር
ሊሰማኝ እስከ ተቻለኝ ድረስ አደራው የእናትዎ ነው። ትልቅ እናት፣ ካገር የበለጠ ምን አለ? ነፍሳቸውን ይማር፣፡

ይህን ምኞትዎን ተግባራዊ ወደማድረጊያው ሲወስዱን የሆድም የራስም በሽታ አሳደሩብኝ፣፡ ኢትዮጵያችን የመኻከለኛው ምሥራቅ የዳቦ ቅርጫት ልትኾን እንደምትችል ሲነገር እንደቆየ ትምሕርት ቤት የገባነው ኹሉ እናውቃለን። እናምናለንም። ይኽ ሳይኾን ቀርቶ ዳቦ ለማኝ የኾነችው ቀበሮና አይጥ እንኳን ጉድጓድ ሲኖሯቸው የኢትዮጵያ ልጆች የራሳቸው ማስገቢያም ማጣታቸው መኾኑን ማንም ያውቀዋል።

ልጆችዋ በዚህ ዓይነት ተወጥረው ባሉበት ጊዜ መጀመርያ ለጅቡቲ፣ ከዚያም ለ ፕረዜዳንቷና ለባለቤታቸው መሬት መሰጠቱን በአንጀት ማረር ሰማነው።የምግብ ዓይነቶችን በብዛት አቅራቢዎች የኢትዮጵያ ገበሮዎች ነበሩና! ከዚያ መሬት መታደላቸውን ስንሰማ፣ ሳልሰማ ማለት ይሻል ይኾን? ሳውዲዎች አገራችን ውስጥ ሩዝ ማምረታቸውን ለእነሱ የምሥራች ለሌላው ግን መርዶ ደረሰ። ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት። ኢትዮጵያም አንጀትዋ እያረረ ዝም አለች። የዝምታን ትርጉምና የሕዝብን ስሜት አበክረው የሚያከብሩ የነበሩት እምዬ ምኒልክ አንድ ሕግ ሊያወጡ ሲያስቡም ኾነ ስው ሲሾሙ አስቀድመው ያስወራሉ። ሰው ከወደደው ያደርጉታል ካልወደደውም ያስቀሩታል። አንድ ጊዜ ስለአንድ ጉዳይ አስወርተው ስዉ ዝም አለ። ቆየት ብለውም ቢጠይቁ አ ኹንም “ @ዝም @ ኾነ እምዬ ምኒልክም “ ዝምን ፍራልኝ!” አሉ ይባላል

ርስዎ ደግሞ ጋምቤላ- ኦሮሞ- አማራ - ሓረር አፋር ደቡብ ወዘተ ሲሉ ትግራይን አለወትሮው አስቀርተው የገልፍና የሳውዲ ሃብታሞች በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በማፍሰስ የርሻ ልማቱ አገሪቱን በሰብል እንደሚያጥለቀልቋት በመፈንጠዝ ሲናገሩ። “ አገሪቱን ለውጠው ለማየት ምኞቴ ነው።” ያሉት ትርጉም አንድምታ እያኾጎደጎደ መጣ። ኾኖም ልብ የሚያሞቀውው “ ኢትዮጵያዊነቴን ማንም አይፍቀውም። ምንም አይገፋውም ” ያሉት እኔን አሸነፈ።

ታዲያ ይህን የአገራችንን የርሻ መሬት በሙሉ ማለት አይቻልም? ይህ ኹሉ መሬት ለሌሎች የመስጠቱን ጉዳይ ከአጼ ቴዎድሮስ የአቧራ ስስት ጋር እንዴት ያጣጥሙታል? ስጦታ አይደለም እንዳይሉኝ አደራ። ' ሊዝ ' የሚባለው ዕዳ ለስንት ዓመት ነው? አኹን በሃአይማኖት ምክንያት ላለው ቀውስ መባባስ ምን ሚና ይጫወታል ይላሉ?

የጀኔራል መንግሥቱንም የመጨረሻውን ጥቅስ ላምጣልዎ።
<u>" ዕውን የክቡርነታቸው በኅይወት መቆየት በዚህ መንግሥት የሚፈለግ ነበር?" እንዳሉ</u>
<u>አኹንስ፦ ዕውን ኢትዮጵያ ከችጋር እንድትላቀቅ የሚፈልግ አለ? ካለ በቀደምት የመሬቱን ባለቤትነት ማረጋገጡ አብነቱ አልነበረም? በጃንሆይ ጊዜ ድርቅ ያጠቃው ግማሽ ሚሊዮን ወገናችንን ሲኾን በዚያን ጊዜ ረዳቶቹ እንዳሉት ቶሎ ካልተቀጨ እስከ አንድ ሚሊዮን ይደርሳል ነበር።</u>

በደርግ ጊዜ የተራቡት ወገኖቻችን ቁጥር ስድስት ሚሊዮን ሲደርስ ዓለም እንደተረባረበልን በባለዉለተኛነት እናስታውሰዋለን። ይህ በኾነበት ጊዜ መሬት ከተወረሰ ስድስት ዓመት፤-ጦርነት ከዳር እስከዳር ሕዝቡንና ደርግን የወጠርበት የምዕራብ ርዳታ ፋይዳ ያልነበረው መኾኑንም ማጤን ይጠቅማል።

ሼኩ ለብዙ ወገኖቻችን እንጀራ ያወጡ፦አንዳንድ ጊዜ የጣላቸውንና ስምና ኪስ ያልተገናኘላቸውን እንዳሳከሙና እንደረዱም ጆሮዬ ባዳ አይደለም የቅርቡና ትልቁ በብዙዎች ዘንድ ክብር ያሰጠዎ የሕጻናት የልብ ሓኪም ቤት መኾኑን በምስጋና ስዘከር ለአገራችንም ስፖርት ያደረጉትን ባለመርሳት ነው። ይባርክዎ!

ከዕቅድዎ ጋር አያይዘው ሲናገሩ " የሳውዲ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት " ሃይ አፕሪሽዬሽን…" አለው ያሉትን " አፕሪሽዬሽን ብቻ፡!" የሚል እንደማይጠፋ አይዘነጉትም።

ይህን ኹሉ የወተውትሁት መነሺያዬ ላይ የአደረብኝን ጭንቀት ይቀንሱልኛል እንዲያውም " ኢትዮጵያ ውስጥ ድህነትን ተረት አደርገዋለሁ ያሉትና ለዚሁም ያለዎት ዕቅድ " ኢትዮጵያን የእስላም አገር እንዳይደርጋትና" እዚያም ለመድረስ የሚደርሰውን በማስታወስ " በሬ ጭዱን እንጂ ገደሉን አላየም" የሚባለው እንዳይደርስብን አስቀድመን መቅጨት ያልብን ይመስለኛል። ይመስለኛል አይደለም " በቁርጥ አለብን ነው!" ርስዎ የተወለዱት በኹለት ሃይማኖት ተከታዮች ውስጥ ነው፡ ያደጉትና የሚኖሩትም። ለኢትዮጵያ ያለዎትን ፍቅር ለኢትዮጵያ ያልዎትም ምኞት " በመጀመርያ ሰላምና ጤንነት ቀጥሎም ከሕዝቡ ጋር በሰላም መኖርን" እንደኾን አበክረው ሲናገሩ " ኢትዮጵያዊነቴን ማንም አይነካውም ማንም አይገፋውም" ያሉትን ዕውን ሊያደርጉ የሚችሉት ከተለያዩ ከአረብ አገሮች ሊያስፈስሱ የተዋዋሉትን መዋዕለ ንዋይ ሲረሱት ሲያስቀሩት ብቻ መኾኑን ሳስትውስዎ " ከእንዴት ዓይነት ክፉ ስህተትና ጥፋት አዳነኝ" እንደሚሉ ተስፋ አለኝ፡፤ አበው " ለ አንበሳ አይመትሩም ለብልህ አይመክሩም" ይሉ የለ? በሥራ ብዛትና በሌላ-ሌላ ጉዳዮች መዋከብ ቀልብን ሊዘርፍ ይችላልና እስከታረመ ድረስ ምንም አይደል፤፡

የርሻ ልማቱን ከውጪ ሳያስገቡ እግዚአብሔር በሰጠዎት ራስዎ አድርገው ቅዱስ ዓላማዎን ሊያሳኩ ይችላሉ። በሰሜን በኩል "ደንበር ካልተካለልን ርዳታ አናገኝም " ሲባል አገር ወዳዱ  የትግራይ ወገናችን " ኢትዮጵያ ድሃ ነኝ ብላ መሬቷን ሰጥታ አታውቅም በኛም አይጀመርም " ( ቃልበቃል ባልጠቅሰውም) ብለው በወሰዱት አኩሪና ቆራጥ አቅዋም የጊዜያዊም ቢኾን በሰሜን በኩል ያለው እንዳለ አለ!

ኢትዮጵያዊነትዎና ለኢትዮጵያ ያለዎ ፍቅር አበረታቶኝ በቅንነትና በስጋት ማስታወሴን ተቀብለው ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ተስፋ አልኝ።

ሼኩ፦ አኹን የኢትዮጵያዊነትና የሙስሊም ልጆችዎ በኢትዮያውያን ክርስቲያን ልጆችዎና በአገርዎ ቅርስ ላይ የጀመሩትን በምድር የወጀል በሰማይ የኩነኔ ዕኩይ ተግባራት " ሳይቀጣጠል በቅጠል" እሚባልቤት ደረጃ ላይ እያለ የመቅጨት ዕድል ከማንም የበለጠ ርስዎ አለዎት ብዬ ከልብ አምኜ ልቀጥል። እስካሁን ሳይባባስ የቆየው በሽማግሌ ሙስሊሞች ልፋትና ድካም መኾኑን በልባዊ ምስጋና በመዘከር ጥረታቸውም ዳር ለማድረስ ይተባበሯቸው፤፡ ሃሳብ ሃሳብን ይወልዳል እንደሚባለው በግርድፉ ልወርውርልዎና ያልሙት

- ከኹለቱም ሃይማኖቶች ጓምያ-ጓምያ ሰላምንና ፍቅርን የሚወድዱትን ሊደመጡም የሚችሉትን የፈለጉትን ቁጥር ይዘው በመመካከር ስልታችሁን አቀነባብራችሁ በመጀመርያ በመገናኛ ብዙሓን የነበረውን የተጀመረዉን ቢቀጥል የሚአስከትለውን ማስተማር
- ወደየክፍለ-አገሩ በመጓዝ በዋና ዋና ከተሞችና ሕዝብ በሚበዛባቸው ከተሞች ኹሉ ከየከተሞቹ ተመሳሳይ አዛውንትን በመጨመር ማስተማር
- ከየክፍለ-አገሮች የተመረጡት አዛውንት በየወረዳዎችና በየቀበሌዎች ትምሕርቱንና ምክሩን መቀጠል  ይህ ኹሉ በመገናኛ ብዙሓን መሪ ስፍራ ተሰጥቶት መዳጋገም
- በአዛውንት ሙስሊሞች ከመባባስ መዳኑ ተጠቅሷል፡፤ ይህ ትብብር እስከመጨረሻው እንዲቀጥልና ውጤቱ እንዲያምር በዚህ ዕኩይ ተግባር ላይ የተሠማሩትን ዘመዶቻቸው፦ጎረቤቶቻቸው እንደሚያውቋቸው ብዙ አያጠራጥርም። አሳልፎ ለወንጀል መስጠት ግን ቢቸግራቸው ሰባዊነት ነው። ስለዚህ ልጆቻቸውን ሲጠቁሙ ሊታሠሩ ሊገደሉ ሳይኾን ሊማሩ ሊሠለጥኑ ምያ ሊይዙ መኾን አለበት። በዚህ ዓይነት አገር ወገንን እስቲ አድኑ
- በየ ሥፍራው እንዳመናችሁበት ንኡስ ደርጎችን አቋቁሞ ግንኙነትን ማጠንከር ወዘተ

- እንደኔ ይኽ መሠራቱ የሚጠቅመው በመጀመሪያ ደረጃ በምዕመናን ቢኾን የሚሻል ይመስለኛል
- የየሃይማኖቶቹ መሪዎች ሚና ምን ሊኾን እንደሚችል( ሰሚ ካለ) በሌላ ጽሑፍ እምክራለሁ

ሼሁ -ይህን በጎደለ ሞልተው ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ከኾኑ ሥልጠናውን በተምለከተ አንዳንድ ሃሳብ ልወረውር እምክራለሁ

ግጥም እውድዳለሁ ብለው አልነበረም? ወደ ልጅነታችንና ውለተታቸው ምን ጊዜም ሊረሳ ወደማይገባው ወደ ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤልና ታሪክና ምሳሌ ልመልስዎ። በርስዎ ጊዜ ቀርቶ ከነበረም አይጎዳም

ኹለት አፍ ያለው ወፍ

.... ያ ግፈኛው ይቅርብህ ቶሎ ጣል
ይህ መርዘኛ ፍሬ መሞትን ያመጣል።
አትብላ እንሞታለን ይህን መርዝ ፍሬ
ይቅርብህ አትብላ አንድንም ዛሬ
የሚያዋዛ አይደለም ይቅር ተው አትበድ
እያለ ደንግጦ ፈርቶ ሲርበደበድ
ያ፡ ግን የቀድሞውን ቂሙን ስላልረሳ
እሞታለሁ ብሎ ለነፍሱ ሳይሳሳ
ብድር መመለሱ ሆነለት ደስታ
ፈርቶ የሚጥለው ፣መስሎ ያመነታ
ቆይቶ በፍርሃት ያንን ሲያንገላታ
ኋል ግን ነቅንቆ ራሱን በእንቢታ
ፍሬውን በላና ከነሁለት አፉ
እዚያው ሳይነሳ ወዲያው ሞተ ወፉ...

ኬኢትዮጵያዊነት ሰላምታዬ ጋር

አሰፋ ሰይፉ

-